# የወላጆች የምዘና መመሪያ

## PSAT

ምዘናዎች ተማሪዎች የክፍል ደረጃን እና የይዘት መስፈርቶችን ያሟሉ መሆናቸውን እንዲሁም ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ተዘጋጅተው ለመመረቅ በመንገድ ላይ መሆናቸውን በተመለከተ ለተማሪዎች፣ ለወላጆች እና ለአስተማሪዎች ጠቃሚ መረጃ ይሰጣሉ። እነዚህ ምዘናዎች የልጅዎን አካዳሚያዊ እድገት ከሚጠቁሙ በርካታ መረጃዎች መካከል አንዱን መለኪያ ለማቅረብ የታሰቡ ናቸው።

### ይህ ምዘና ምንድነው?

የቅድመ SAT (PSAT) በዘ ኮሌጅ ቦርድ (The College Board) የተዘጋጀ፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለSAT ለመዘጋጀት እንዲረዳቸው የሚወሰድ እንዲሁም ለብሔራዊ ሜሪት የስኮላርሺፕ ፕሮግራም (NMSQT) ብቁ ሊያደርጋቸው የሚችል ወጥነት ያለው ፈተና ነው። የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች PSAT 9ን ይወስዳሉ። የአሥረኛ ክፍል ተማሪዎች PSAT 10ን ይወስዳሉ። PSAT አሁን በዲጂታል የሚሰጥ ሲሆን፣ የወረቀት ፈተናን እንደ ማመቻቻ የሚያመለክት IEP ላላቸው ተማሪዎች በወረቀት የሚሰጥ አማራጭ አለው።

የቅድመ SAT (PSAT) የተማሪዎችን ክህሎትና እውቀት በተመለከተ ግንዛቤ የሚሰጥ ሲሆን፣ ይህም ግላዊ የSAT ታላሚ ውጤቶችን እንዲያወጡና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ ስለሚሄዱበት የትምህርት መስመር በመረጃ የተደገፉ ውሳኔዎችን እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል።

የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች PSAT 9ን ይወስዳሉ። የአሥረኛ ክፍል ተማሪዎች PSAT 10ን ይወስዳሉ።

### ልጄ የሚፈተነው/የምትፈተነው መቼ ነው?

የPSAT ምዘና የሚሰጠው በኤፕሪል ወር ሲሆን በሁለት ሳምንት የፈተና ጊዜ ውስጥ ይከናወናል። ይህ የፈተና ጊዜ የሚከናወነው በኤፕሪል ወር አጋማሽ ላይ ነው። ተማሪዎች በፈተናው መስጫ ቀናት በየዕለቱ ፈተና አይወስዱም ይልቁንም በተወሰኑ ቀናት እና ጊዜያት ይፈተናሉ። ትክክለኛውን የፈተና መርሃ ግብር ለማወቅ እባክዎ የልጅዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ።

### እነዚህ ውጤቶች ጥቅም ላይ የሚውሉት እንዴት ነው?

የPSAT 8/9 እና የPSAT 10 ውጤቶች ከPSAT/NMSQT በተለየ መልኩ ጥቅም ላይ የሚውሉ ሲሆን፣ በአብዛኛው እንደ የምርመራና የዕቅድ መሳሪያዎች ሆነው በሚከተሉት ዘርፎች ያገለግላሉ፦

- ለአካዳሚያዊ እድገት ክትትል

- ለቀደምት ድጋፍና እገዛ
- ለኮርሶች ዕቅድ

## ተጨማሪ መረጃ

በልጅዎ ትምህርት ውስጥ እንዲሳተፉ እናበረታታዎታለን። እባክዎ ልጅዎን በቤት ውስጥ እንዴት መርዳት እንደሚችሉ እና ልጅዎ ብቁ ከሆነ/ች የፈተና ማመቻቻዎች መኖራቸውን በተመለከተ ጥያቄዎች ካለዎት የልጅዎን አስተማሪ ለማነጋገር አያመንቱ።

- **የDPS PSAT ድረ ገጽን** ይጎብኙ
- የኮሌጅ ቦርድ የወላጅ መርጃ ሀብቶችን ይጎብኙ

ተጨማሪ መረጃ፦ ምዘናዎች

**assessments.dpsk12.org** ን ይጎብኙ

ስለ ምዘናዎች ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉዎት እባክዎ የልጅዎን ትምህርት ቤት በቀጥታ ያነጋግሩ ወይም ለቤተሰብ እና ማህበረሰብ ተሳትፎ በስልክ ቁጥር 720-423-3054 ይደውሉ።